# ዕንባ ጠባቂ፣ዜጎችና መልካም የመንግስት አስተዳደር

........................................

መልካም አስተዳደር መልካም ካልሆነው ስመለየት ሲባል መልካም አስተዳደር የሚለው ሀረግ እንደተፈጠረ የተለያዩ ፅሁፎች ያስረዳሉ :: መልካም አስተዳደር በዋናነት የሚተረጎመው ከውሳኔ መስጠት ሂደትና የተወሰነውን ውሳኔ ከማስፈፀም ሂደት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ስለሆነም ለዜጎች ፍላጎት ተገቢ ምላሽ የሚሰጡ፣የህዝብ መብቶች የሚያስጠብቁ፣ አገልግሎት የሚያቀርቡና ፖሊሲዎችን በብቃት ተግባራዊ የሚያደርጉ የአስተዳደር ስርዓቶች መልካም አስተዳደር /Good governance/ ሲባል ከዚህ በተቃራኒ ገፅታ ያለው ደካማ አስተዳደር /Poor governance/ በመባል ይጠራል፡፡

የአንድ ሀገር ዲሞክራሲያዊነትና የአስተዳደር ስርዓት የሚመዘነው የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን በምን ያህል መጠን ወይም ደረጃ ተግባራዊ እንዳደረገ ነው፡፡ የሀገራት ዘላቂና የተስተካከለ እድገትና ህልውና የሚወሰነውም እነዚህን መርሆዎች ተግባራዊ በማድረግና ባለማድረግ ላይ እንደሆነ የፖለቲካ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ የመልካም አስተዳደር መርሆዎች የሚመነጩት ከህገመንግስቱ ሲሆን ህገመንግስቱ መልካም አስተዳደር የሚለውን ሀረግ በቀጥታ ባይጠቀምም ሁሉንም መገለጫዎቹን ግን በልዩ ልዩ አንቀፆች እንዲካተቱ አድርጓል፡፡ ስለዚህ የመልካም አስተዳደር ጉዳይ የህገመንግስት ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የመንግስት አስተዳደር የሚያወጣቸው ደንቦችና መመሪያዎች ተቀባይነት የሚኖራቸውና የሚያስተሳስፏቸው ውሳኔዎች የሚፈፀሙበት የህብረተሰብ ፍላጎት ማዕከል ያደረጉ ሲሆኑ ነው፡፡ በመንግስት አስፈፃሚ አካላት የሚወሰኑ ውሳኔዎች፣ የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ደግሞ የህብረተሰቡን ፍላጎት ያማከሉ መሆናቸው የሚረጋገጠው የመንግስት አስተዳደሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን በቀጥታ ወይም በተወካዮች አማካኝነት ማሳተፍ ሲችል ነው፡፡

የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ደግሞ በተሻሻለው አዋጅ 1142/2011 የሰዎች ህገመንግስታዊ መብቶችና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት እንዲከበሩ የህግ የበላይነትን መሰረት ያደረገ ጥራት፣ቅልጥፍናና ግልፅነት ያለው መልካም የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን ለማድረግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚሰራ ተቋም ነው፡፡

በዚህም መሰረት ተቋሙ አስፈፃሚ አካላት የሚያወጧቸው ህጎች ፣ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም አሰራሮቻቸው ከሰዎች ህገመንግስታዊ መብቶች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥና የዜጎች አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም ላይ የተለያዩ የጥናትና የቁጥጥር ስራዎችን በማከናወን እንዲሁም አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዳይፈፀሙ በመከላከልና አስተዳደራዊ በደል የደረሰባቸው ሰዎች አቤቱታ

በመቀበልና በመመርመር የዕርምት እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ መልካም የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን እየሰራ ይገኛል፡፡

መልካም አስተዳደር የሚሰፍነው ደግሞ መንግስት ህገ መንግስቱን መሰረት ያደረገ ግልፅ መርሆዎችን እና አሰራሮችን ሲዘረጋ እና ዜጎች የህግ የበላይነት ሰፍኖ ቀልጣፋ አገልግሎት ሲያገኙ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከሰፈነና መልካም የመንግስት አስተዳደር መዘርጋት ከተቻለ ሰዎች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በነፃነትና በቀላሉ በመሳተፍ ለሀገራቸው የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ዜጎችም/ዜጎች ከአስፈጻሚ አካላት ጋር በሚያደርጉት የዕለት ተዕለት ግንኙነት የሚያዩዋቸውን እና የሚያጋጥሟቸውን የአስተዳደራዊ ግድፈቶች እንዲታረሙ ከህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ጎን በመቆም የበኩላቸውን ሚና መጫወት የጠበቅባቸዋል ፡፡ ይህም ሲሆን በደሎችና ኢ- ፍትሃዊ አሰራሮች ይቀንሳሉ፤ በዛው ልክ የዜጎች መብቶች ይከበራሉ ሲቀጥልም የማህበራዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶቻቸው ይሟላሉ ከዚህም ጎን ለጎን ዜጎች በሚዲያ እና በሌሎች መሰል ግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶች ስለዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት ግንዛቤያቸው እየጨመረ ሲሄድ በማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እንዲሁም በልማት ላይ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የበኩላቸውን አስተዋፅዎ ያበረክታሉ ለዚህ ደግሞ ተቋሙ በመልካም የመንግስት አስተዳደር ዙሪያ ዜጎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ያሳሰለሰ ጥረት እያደረገ ይገኛል ለወደፊቱም ይህንን አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

ተቋሙ ይህንኑ ተግባር በሚገባ እንዲወጣ በአንድ በኩል ህብረተሰቡ መብቱን ብቻ ሳይሆን ግዴታውንም በሚገባ በመገንዘብ ድጋፉን በሚሹ ተግባራት ላይ በንቃት በመሳተፍ የበኩልን ሚና መጫወት የሚገባው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መረጃ የሚፈልግበት ጉዳይ ካለ በአግባቡ በመጠየቅ ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ በመልካም አስተዳደር ግንባታ የዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ የሚጎለብተው፣ በመንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ የተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት የበኩላቸውን ድጋፍ ሲያደርጉ መሆኑ እሙን ነው ይህንኑ ከግብ ለማድረስ ህብረተሰቡ በራሱ ስለመብቱና ስለግዴታው እንዲሁም ስለመልካም አስተዳደር አስፈላጊነትና ጠቀሜታ በመረዳት ከታችኛው እስከ ላይኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታል ፡፡

በአጠቃላይ የእነዚህ መርሆዎች መተግበር ድምር ውጤት ዜጋው የሚያገኘውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ከማድረጉም በተጨማሪ የተጀመረውን ሀገራዊ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ እና የተሳለጠ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር በማድረግ ያሳሰለሰ ሚና ይጫወታል ፡፡ ከዚህም በመነሳት የመልካም አስተዳደር መስፈን፣ ለአንድ ዴሞክራሲያዊ አገር የውዴታ ግዴታ በመሆኑ ልንተገብረውና ለመርሆዎቹ መተግበርም ደግሞ ከተቋሙ ጎን በመቆም ሁላችንም የበኩላችንን ሚና መጫወት ይጠበቅብናል ፡፡

## መልካም የመንግስት አስተዳደር ከማስፈን አንፃር የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምና የቅሬታ ሰሚ አካላት ሚና

……………………………………………

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም መልካም የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን ስማድረግ በማቋቋሚያ አዋጁ 1142/2011 ከተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት መካከል አስተዳደራዊ ጥፋትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መቀበልና መመርመር አንዱ ነው፡፡ በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚስተዋለው የመልካም አስተዳደር ችግር እና የሚቀርቡ ቅሬታዎች ዘርፈ ብዙ እና መጠነ ሰፊ እንደመሆናቸው መጠን የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በዜጎች ላይ አስተዳደራዊ በደል እንዳይደርስባቸው በመከላከልና ዜጎች ተበድለው እንዳይቀሩ ስማድረግ ይሰራል፡፡

በአሁኑ ወቅት መልካም የመንግስት አስተዳደር ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ በመምጣቱ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ያለው የመልካም አስተዳደር አገልግሎት አሰጣና አተገባበር ሁኔታ በትኩረት እየተሰራበት ያለና ወቅታዊ አጀንዳ ሆኗል፡፡ በአንጻሩም የዜጎች የተገልጋይነት ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ በመንግስት ተቋማት ውስጥ በርካታ ቅሬታና አቤቱታ እየተስተናገደ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ይበልጥ ወደ ሕብረተሰቡ በመውረድ ቅሬታዎችን በወቅቱ፣በተገቢውና በባለቤትነት ስሜት ሙሉ ጊዜያቸውን ለዚህ ተግባር በማዋል የሚያስተናግዱና መፍትሄም የሚሰጡ የመንግስት አካላት በእያንዳንዱ መንግስታዊ ተቋም ማቋቋም አስፈላጊነቱ ታምኖበት እንቅስቃሴ ውስጥ ከተገባ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ይህንኑ ዓላማ ከግብ ለማድረስም በዋናነት የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር እንዲሁም ተደራሽነት ለማሳለጥ በየክልሉካሉ የቅሬታ ሰሚ አካላት ጋር በመቀናጀት የቅሬታ ማስተናገጃ ስርአቱን በማገዝና እንዲጠናከሩ በማድረግ አብሮ እየሰራ ይገኛል ፡፡ በመሆኑም ይህንኑን የሚያሳልጥ አሰራር መዘርጋትን ይጠይቃል ፡፡ የሥርዓቱ መዘርጋትና መጠናከር ደግሞ ብልሹ አሠራርን ከመነሻው ማስወገድ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ ከቅሬታ ሰሚ አካላት ጋር ፈጣን የመረጃ ልውውጥ እና የስራ ግንኙነት በማድረግ ተቋሙ በአዋጅ የተሰጠውን መልካም የመንግስት አስተዳደርን የማስፈን ዓላማ ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡

በተጨማሪም የቅሬታ ሰሚ አካላት መቋቋም ከሚያበረክታቸው በርካታ ጠቀሜታዎች አንዱ ተገቢ ያልሆነ ወጪን ማስቀረት መቻሉ ነው፡፡ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ቅሬታዎችን የማስተናገድ፣ህብረተሰቡ ቅሬታውን በአቅራቢያውና ያለእንግልት አገልግሎት በማግኘት የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈቱ ያስችላል ፡፡ ስለዚህ የቅሬታ ሰሚ አካላትን ማቋቋምና ማጠናከር ወጥ የአሰራር ስርዓትን ከመዘርጋት ባሻገር ህብረተሰቡ የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ፡፡

በሌላ በኩል በመንግስት መስሪያ ቤቶች ለተጠቃሚው ህብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡ

ሃላፊዎች እና ፈጻሚ ባለሙያዎች ለሚሰጡት አገልግሎት ሃላፊነትና ተጠያቂነት እንዳለባቸው ማረጋገጥ አንዱ የመልካም አስተዳደር መገለጫ ነው፡፡ የተጠያቂነት አሰራር በዋነኛነት ፋይዳው የሚለካው በተገቢው ሁኔታ የታቀደና በጥንቃቄ የሚመራ የቅሬታ አሰማምና አፈታት ስርዓት በሚፈለግበት ቦታ ሁሉ መዘርጋት ሲቻልና በዚህም ተገልጋዩ ህብረተሰብ አገልግሎት በሚያገኝባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ ያለው አመኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሄድ ነው፡፡



ዋና ዕንባ ጠባቂ መድረኩን ሲመሩ

በዚሁ መሰረት የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በክልልና በየደረጃው ካሉ የቅሬታ ሰሚ ቢሮዎች ጋር በመስራት፣በመደገፍና ተጠያቂነት ያለበት አገልግሎት እንዲሰፍን በማድረግ ወደ ተቋሙ የሚመጡ አቤቱታዎች በመቀነስ፤ህብረተሰቡ ቅሬታውን በአቅራቢያው እንዲፈታለት በማገዝ መልካም የመንግስት አስተዳደር በመገንባቱ ሂደት የተጣለበትን ሀላፊነት እየተወጣ የሚገኝ ሲሆን ለወደፊቱም ይህንኑ ተግባር አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡



የመድረኩ ተሳታፊዎች በከፊል

ተቋሙ ለከተማው ህብረተሰብ የሚቀርበው ውሀ ተመጣጣኝ አለመሆኑን ገልፀ፡፡

...............................................



የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን መስሪያ ቤትና ሁለት ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች ላይ ቁጥጥር አደረገ፡፡

በቁጥጥሩ ወቅት ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩም የተለያዩ የህግና የአሰራር ክፍተቶች ተለይቶ የመፍትሄ ሀሳቦችም ያስቀመጠ ሲሆን የመፍትሄው አካል መሆን ያለባቸው ተቋማት በዝርዝር ተጠቁሟል፡፡

ከተለዩ የህግ ክፍተቶች መካከል የኮንዶሚኒየም ቤቶች፣ የቤቶች ኤጀንሲና የሪልስቴት ባለቤቶች ከባለስልጣን መስሪያቤቱ ጋር ያላቸው የስራ ግንኙነቶችን በተመለከተ ግልፅ የሆነ መመሪያዎች ያለመኖር ሲጠቀስ ከታዩ የአሰራር ክፍተቶች መሀከል የመንግስት የኪራይ ቤቶችና ሰነድ አልባ ቤቶችን የውሀ ታሪፍ መመሪያዎች ወቅቱን ባማከለ መልኩ አለመሻሻል፣የውሀ ምርቱ ከፍላጎት ጋር አለመጣጣም፣የውሀ ስርጭት ፍትሀዊ አለመሆን፣የህብረተሰቡ የፍሳሽ ይነሳልኝ ፍላጎትና አገልግሎት የተመጣጠነ አለመሆን፣ ከመብራት ሀይልና ከቴሌ ጋር ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር፣ቆጣሪ ማንበብ ላይ ባንዳንድ ሰራተኞች የዲሲፕሊን ጉድለት መኖር፣በመስመር ዝርጋታ ወቅት የሚቆፈሩ ቦዮችን ቶሎ ያለመደፈን፣ የመስመር ብልሽት ጥገና ፈጣን አለመሆኑና የውሀ ብክነት መኖር በቁጥጥር ወቅት ከተለዩት ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ተቋሙ ያስቀመጠውን የመፍትሄ አቅጣጫ ተግባራዊ በማድረግ ህብረተሰቡ ከውሃ ጋር ተያይዞ የሚያነሳቸውና የሚፈጠሩ በርካታ ችግሮች ባፋጣኝ ማረም ይጠበቅበታል፡፡

ትምህርት ቤቶች በመልካም ስነ ምግባር የታነፀ ዜጋን ከመፍጠር አንጻር ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተገለፀ

.........................................

የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ከሰባት ክልሎች በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ላይ የመልካም አስተዳደር ክበባትን በማቋቋም የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ተሰጠ፡፡

ተቋሙ በአዋጅ ከተሰጡት ተግባርና ሃላፊነቶች ውስጥ አንዱ ህብረተሰቡ ስለመልካም አስተዳደርና ስለአስተዳደራዊ ፍትህ ግንዛቤ እንዲኖረው የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ግንዛቤ መፍጠር ነው፡፡

በመሆኑም ተቋሙ የመልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና በዜጎች ላይ የሚደርሰውን የአስተዳደር በደል ለመከላከል በ7 የክልል ከተሞች ላይ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የመልካም አስተዳደር ክበባትን በማቋቋም ለትምህርት ጽህፈት ቤት ሃላፊዎች፣ ለርዕሰ መምህራን፣ ለመልካም አስተዳደር ክበባት አስተባባሪ መምህራንና ተማሪዎች የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ሰጥቷል፡፡

እንዲሁም በደቡብ ክልል በወላይታ ሶዶ ከተማ ከተመረጡ በሁለት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ ርዕሰ መምህራን፣የክበቡ አስተባባሪ መምህራንና ለመልካም አስተዳደር

ክበባት ተማሪዎች የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በስልጠናው ስለ ተቋሙ ተግባርና ሃላፊነት፣የመልካም አስተዳደር ክበባትን ከማጠናከርና ቀጣይነቱን ከማረጋገጥ አንጻር ከኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ የርዕሰ መምህራን፣የክበቡ አስተባባሪ መምህራንና ተማሪዎች ሚና ላይ ሰነዶች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

ትምህርት ቤቶች በመልካም ስነ ምግባር የታነፀ ዜጋን ከማፍራትና ስለመልካም አስተዳደርና ስለአስተዳደራዊ ፍትህ ግንዛቤ በመፍጠር በዜጎች ላይ የሚከሰቱ የአስተዳደር በደሎችን ለመከላከልና በሃገሪቱ የመልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ ለማስቻል ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የመልካም አስተዳደር ክበባት ተማሪዎች ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠሩ በኩል ትልቅ አስተዋጾ ያበረክታሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል እነዚህ ክበባት አጠናክሮና ወጥነት ባለው መንገድ ለመምራትና በተቋሙ ስልጣንና ተግባራት ዙሪያ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያገለግል የተማሪዎች ማሰልጠኛ ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡፡



አቶ ዘውዱ ወንድም ስልጠና ሲሰጡ



የተማሪዎች ማሰልጠኛ ሰነድ ዝግጅት በከፊል

## መረጃ በማይሰጡ የተቋማት የበላይ አመራሮች ሳይ የተጠያቂነት አሰራር ሊኖር ይገባል ተባለ

.............................................

የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባሉ ተቋማት ውስጥ ከሚሰሩ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች ጋር በመረጃ ነጻነት አዋጅ አተገባበር ዙርያ በአዳማ ከተማ ውይይት አድርጓል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዋና እንባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ ኃይሌ በውይይቱ ወቅት እንደተናገሩት የመረጃ ነጻነት ህግን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 590/2000 ክፍል ሶስት ስር የተደነገጉትንና ለተቋሙ የተሰጡ ሃላፊነቶችን ለማስፈፀም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ተቋሙ በተሰጠው ተግባርና ሃላፊነት መሰረትም ህጉን ለመተግበር የሚያግዙ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች እንዲ,ዘጋጁ ሃሳብ የማቅረብና የመደገፍ፣ መረጃ አትሞ ማሰራጨትን በሚመለከት ግልጽ የአሰራር መመሪያ አዘጋጅቶ በመንግስት ተቋማት እንዲተገበር የማድረግ ፣ለህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎችና አግባብነት ላላቸው አካላት ስለህጉ ይዘት ስልጠና መስጠትና መረጃ ከማግኘት መብት ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለማስተናገድ የሚያስችል ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግና መረጃ የማግኘት መብት ጥሰትን በሚመለከት ተቋሙ የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች በአስተዳደራዊ ይግባኝ አይቶ መወሰንና ሌሎችም ተግባራት ተቋሙ እያከናወነ መሆኑን አክለው ጠቅሰዋል፡፡

ዋና እንባ ጠባቂው አያይዘውም ተቋሙ ከህዝብና መንግስት የተጣለበትን ሃላፊነት ለመወጣት የመረጃ ነጻነት ህጉን በማስተግበር ረገድ በርካታ አበረታች ስራዎች መሰራታቸውን ገልፀው በሃገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ስኬታማ መሆን የሚቻለውና ዜጎች መረጃ የማግኘት መብታቸው የሚረጋገጠው ራሱን በከፍተኛ ስነ-ምግባር በማነፅ በከፍተኛ ሙያዊ ብቃት የሚንቀሳቀስና ለህዝብ የወገነ የመገናኛ ብዙሃን ሲኖር ፣ ሙያቸውን በአግባቡ የሚወጡ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎችና የመረጃ ነጻነት አዋጁን በትክክል የሚተገብሩና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ የሚወጡ የተቋማት የበላይ አመራሮች የጋራ ቅንጅት መሆኑን በመጥቀስ የዜጎችን መረጃ የማግኘት መብት በማስከበር በሃገራችን ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን ተናገረዋል፡፡

የውይይቱ ተሳታፊዎችም በበኩላቸው ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን ያነሱ ሲሆን የመረጃ ነጻነት አዋጅን በተቋማት ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የተቋማት የበላይ አመራሮች ስለ መረጃ ነጻነት አዋጁ ግንዛቤ ሊፈጠርላቸው ይገባል፤የዜጎች መረጃ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ መረጃ በማይሰጡ የተቋማት የበላይ አመራሮች ሳይ የተጠያቂነት አሰራር ሊኖር ይገባል፤ በየተቋሙ የሚገኙ የህዝብ ግንኙነት አደረጃጀት ወጥ መሆን አለበት፤በየተቋማቱ የተጠናከረ የመረጃ ማእከል ሊኖር ይገባል፤ የተለያዩ የሚዲያ ተቋማት ባለሙያዎች ከየተቋማቱ የሚወሰዱትን መረጃ በራሳቸው ፍላጎትና ስሜት ብቻ የመዘገብ አዝማሚያ ይታያል፤ዘገባውም ለህዝብ የወገነ አይደለም፤የህዝብ ግንኙነት ለአንድ ተቋም የጀርባ አጥንት ቢሆንም የህዝብ ግንኙነት ባለሙያው በቂ ትኩረት እያገኘ አይደለም፤ ጋዜጠኞች፣ የህዝብ ግንኙነት አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም አስፈጻሚው አካል በተገኙበት በመረጃ ነጻነት አዋጅ አተገባበር ሳይ የጋራ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማዘጋጀት ቢቻል፤ የመረጃ ነጻነት ህጉን በተገቢው መንገድ ለማስተግበር የህዝብ ግንኙነቱ የስራ ክፍል የተቋሙ የማናጅመንት አባል መሆን ቢችል፤የህዝብ ግንኙነቱን መብት ሊያስከብር

የሚችል ማህበር መመስረት ቢቻል የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተነስተው ከመድረኩ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሰነዶች አጠባበቅ፣አስተዳደርና አወጋገድ የተግባር መመሪያ ቁጥር 3/2012 ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡



አቶ ማናዬ አለሙ በመረጃ ነፃነት ዙሪያ ስልጠና ሲሰጡ



የመድረኩ ተሳታፊዎች በከፊል

የትምህርት መገናኛ ማዕከላት ተተኪ ትውልድን በመልካም ስነምግባር ከማነፅና መልካም አስተዳደርን ከመገንባት አንጻር የማይተካ ሚና አላቸው ተባለ፡፡

..........................................

የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ከክልል የትምህርት መገናኛ ማዕከላት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር የተቋሙን ስልጣንና ተግባር ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በትብብር በሚሰሩባቸው ሁኔታዎች ላይ ውይይት አድርገዋል፡፡

በኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የሴቶች፣ ህጻናት፣አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን እንባ ጠባቂ ክብርት ወይዘሮ ሳኒያ ሳኒ በመክፈቻ ንግግራቸው ወቅት እንዳሉት የዜጎች ህገመንግስታዊ መብቶችና ጥቅሞች በአስፈጻሚው አካላት እንዲከበሩ የህግ የበላይነትን መሰረት ያደረገ ጥራት ቅልጥፍናና ግልጽነት ያለው መልካም የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን ለማድረግና ተቋሙ የተጣለበትን ስልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት የባለድርሻ አካላት ሚና ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አክለውም የትምህርት መገናኛ ማዕከላት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተቋሙን ስልጣንና ተግባራት ለተማሪዎችና ለሌሎች አደማጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በማስተዋወቅና በማስተማር በመልካም ስነ ምግባር የታነጸ ዜጋን በመፍጠር ረገድ ጉልህ ሚና ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው ለሚያደርጉት አስተዋጾም የተቋሙ አምባሳደሮች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዘውዱ ወንድም በበኩላቸው ከክልል ትምህርት መገናኛ ማዕከላት ጋር በትብብር የሚዘጋጁት ማስታወቂያዎችና ፕሮግራሞች ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች አስመልክቶ ገለጻ ባደረጉበት ወቅት እንዳሉት ባለፉት 5 ዓመታት ውስጥ ወደ ተቋሙ የመጡ አቤቱታ አቅራቢዎችን መሰረት አድርጎ ከተከፈቱ መዝገቦች ዉስጥ 50 በመቶዉ የሚጠጉት ተቀባይነት ያላገኙ ናቸዉ፣ ለዚህ ደግሞ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም የተቋሙን የስልጣን ገደብ አለመረዳት አንዱ ምክንያት ነዉ፡፡

ስለዚህ ተቋሙ የማይመለከታቸው የሚከተሉትን ጉዳዮች ማለትም :- በህዝብ ምርጫ የተቋቋሙ ምክር ቤቶች በሕግ አውጪነታቸው የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች፣ በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በክልል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በመታየት ላይ ያሉ እና የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን ፣ በፍርድ ቤቶች ወይም በህግ የመዳኘት ስልጣን በተሰጣቸው አካላት በመታየት ላይ ያሉ እና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ፣በመከላከያ ሰራዊትና በፖሊስ ክፍሎች የሚሰጡ የፀጥታ ወይም የአገር መከላከል ጉዳዮች የሚሰጡ ውሳኔዎችን የመመርመር ስልጣን እንደሌለው የትምህርት ቤቶች ሚዲያዎች ለትምህርት ቤቶች ማህብረተሰቡ ማሳወቅ ይገባል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የተቋሙ የምርመራ ዉጤቶችን፣ የቁጥጥርና ጥናት ስራዎችን፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተመለከተ ልዩ ድጋፍን የሚሹ መሆናቸዉን ከግምት ዉስጥ አስገብቶ በልዩ ትኩረት መስራት፣ ነባር ሕጎችን ወይም አሰራሮችን ከማረም እና ከማስተካከልና አንጻር፣ የመረጃ ነፃነት አዋጅን ከማስተግባር አኳያ እንዲሁም አካባቢያዊ ቅኝቶችን በማድረግ ቅሬታ የሚበዛበትን ተቋም ላይ በአካል ተገኝቶ ተገልጋይንም አገልጋይንም መሰረት ያደረገ መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ከክልል ትምህርት መገናኛ ማእከላት እንደሚጠበቅ ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል፡፡

በሌላ በኩል ማስታወቂያዎችና ፕሮግራሞች በእውቀት ላይ ተመስርተው እንዲዘጋጁና መረጃዎችን በትክክል ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1142/2011 እንዲሁም የመረጃ ነጻነት አዋጅ 590/2000 ሰነዶች ላይ ለክልል ትምህርት መገናኛ ማዕከላት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

እንዲሁም በኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምና በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች የስራ ክፍሎች እና የክልል ትምህርት መገናኛ ማእከላት መረጃን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በሚዘጋጁት ማስታወቂያዎችና ፕሮግራሞች በሚኖራቸው ሚና ላይ ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል፡፡



የመድረኩ ተሳታፊዎች ውይይቱን ሲከታተሉ



ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ ሽልማት ሲሰጡ

## የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በቁጥጥር ግኝቶች ሳይ የምክክር መድረክ አካሄደ

..............................

የህፃናት፣ሴቶች፣አካልጉዳተኞችናአረጋዊያን ዳይሬክቶሬት በአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ የቁጥጥር ግኝቶች ሳይ በ24/9/13 በአዳማ ከተማ የምክክር መድረክ አካሄደ፡፡

በእለቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች፣የኢፌድሪ ሰራተኛና ማህበራዊ ሚ/ር መስሪያ ቤትና ቢሮ ሰራተኞች፣ የኢፌድሪ ሴቶችና ህፃናት ሚ/ር ተወካዮች ተስያዩ ማህበራትና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል፡፡

በመድረኩ የሴቶችን ጉልበት የሚጠቀሙ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ከአለም አቀፍ ስራ ህግና ከሀገራችን ህግ አንፃር የሴቶችን መብት ከማስጠበቅና ተጠቃሚነታቸውን ከማረጋገጥ አንጻር እንዲሁም የአረጋዊያን ድጋፍና እንክብካቤ የሚሰጡ የግል ተቋማትን ፍቃድ በመስጠትና ተጠቃሚነታቸውን ከማረጋገጥ አንፃር እንዲሁም የአረጋዊያን ድጋፍና እንክብካቤ የሚሰጡ የግል ተቋማት ዙሪያ የቁጥጥር ግኝቶች የቀረቡ ሲሆን በምክክር መድረኩ የተገኙ አስፈሚ አካላትና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቁጥጥሩ በተገኙ አዎንታዊ ግኝቶች፣ ችግሮች፣ የአሰራርና የህግ ክፍተቶች እንዲሁም በተሰጡ የመፍትሄ ሀሳቦች ሳይ ውይይት ተደርጎ በተነሱ ጥያቄዎች ዙሪያ የህፃናት፣ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ሰብለ ታሪኩ ማጠቃለያ በመስጠትና የሴቶችና አረጋዊያን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ እኩል ተሳትፎና የመብታቸው ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አስፈፃሚ አካላትና ባለድርሻ አካላት ከተቋሙ ጎን በመቆም የበኩላቸውን ሚና መጫወት እንደሚገባቸው ጠቁመው ውይይቱ ተጠናቋል፡፡



ወ/ሮ ሰብለ ታሪኩ መድረኩን ሲመሩ



የመድረኩ ተሳታፊዎች በከፊል

ተቋሙ የራስ ተነሳሽነት ምርመራ ውጤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምክክር አካሄደ

……………………………

የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በተለያዩ ኢንደስትሪ ፓርኮች ፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ላይ የሚፈፀሙ አስተዳደራዊ በደሎችን አስመልክቶ ያካሄደውን የራስ ተነሳሽነት ምርመራ ውጤት ዙሪያ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሰኔ 3/2013 ዓ.ም በአዳማ ከተማ የምክክር መድረክ አካሄዷል፡፡

በመድረኩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የተቋሙ ዋና ዕንባ ጠባቂ ክቡር ዶ/ር እንደለ ሀይሌ እንደተናገሩት በኢደስትሪያል ፓርኮች ፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች መብቶቻቸው እና ጥቅሞቻቸው የማይከበርላቸው ከሆነና በፓርኮች የኢንደስትሪ ሰለም ከሌለ ሰለም አዳመይኖር ተውቆ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለዋል፡፡

ዋና ዕንባ ጠባቂው አያይዘውም ተቋሙ በተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ለተቋሙ በቀረቡት ጥቆማዎችና አቤቱታዎች እንዲሁም በራስ ተነሳሽነት በኢንዱስትሪያል ፓርኮች ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች አስተዳደራዊ በደል እንዳይፈፀምባቸውና ተበድለው እንዳይቀሩ በተለያዩ ፓርኮች ምርመራ በመድረክ የታዩ የህግና የአሰራር ክፍተቶች እንዲታረሙ በማድረግ ረገድ መድረኩ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ገልፃ ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጠው አሳስቧል፡፡

የምርመራ ውጤቱን ያቀረቡት የህግና የአስተዳደር በደል ምርመራ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ መንግስቱ ቀኜ እንደተናገሩትየራስተነሳሽነትምርመራውበኮምቦል ቻ፣በደሴ፣በጂማ፣በሀዋሳ እና በድሬደዋ የተካሄደ መሆኑ ገልፃ በሁሉም አንዳስትሪያል ፓርኮች ፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች የሚፈፀምባቸውን አስተዳደራዊ በደሎች፣የህግና የአሰራር ክፍተቶችን በዝርዝር ቀርበው በመድረኩ ተሳታፊዎችም ሰፊ ውይይት ተደርጎባቻው፡፡ በራስ ተነሳሽነት ምርመራው ወቅት ከታዩት ችግሮች መካከል የደረጃ እድገት፣የዕውቀት ሽግግር፣ አስፈላጊ የሆነ የአቅም ግንባታ ስልጠና አለመስጠት ፣የስራ ቅጥር ውል አለመኖር፣ ዝቅተኛ የደሞዝ መጠን አለመኖርና ወጥ ያለመሆን ፣የአመት እረፍት በአግባቡ አለመሰጠት ፣ከስራ ገበታቸው ያለአግባብ መባረር፣የመኖሪያና የትራንስፖርት ችግር እንዲሁም ምቹ የስራ አካባቢና የስራ ደህንነት አለመኖር እና ወዘተ በምርመራ ወቅት የታዩ የህግና የአሰራር ክፍተቶች መሆናቸውን አብራርቷል፡፡

በመጨረሻም በመድረኩ የተገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተወካዮች ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስተር፣ከሴቶች ህፃናት እና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስተር እና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን መስሪያ ቤቶች የተወጣጡ ጉዳዮች የሚመለከታቸው አካላት አማካኝነት ሰፊ ውይይት በማድረግ ተሳታፊዎቹ ችግሮች መኖራቸውን ገልፃ የታዩ የህግና አሰራር

ክፍተቶች ችግሮች እንዲቀረፉ ተቋሙ ባቀረበው የመፍትሔ ሃሳብ ላይ በጋራ እንደሚሰሩ ከስምምነት ላይ ተደርሷል፡



አቶ መንግስቱ ቀኜ የምርመራው ውጤት ሲያቀርቡ



ተሳታፊዎች ገለፃውን ሲከታተሉ

## መልካም አስተዳደር የሁላችንም ጉዳይ ሊሆን ይገባል

..............................

መልካም አስተዳደር ስሚለው ፅንሰ ሀሳብ ወጥ ትርጉም ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያየ መልኩ ይረዱታል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ምሁራን ተለያዩ መገለጫዎች ይሰጡታል አንድምታው ግን ለአንድ ሀገር እድገት ቁልፍ መሆኑን ይስማሙበታል፡፡ በሌላ መልኩ መልካም አስተዳደር አንድ ጊዜ ተሰርቶ የሚያበቃ ሳይሆን በየጊዜው የሚሻሻልና የማይቋረጥ የአሰራር ሂደትም ነው፡፡ ቀጣይነት ያለው የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ስርዓት ግንባታም ለመልካም አስተዳደር ግንባታ አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1142/2011 መሰረት የሰዎች ህገመንግስታዊ መብቶችና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት እንዲከበሩ የህግ የበላይነትን መሰረት ያደረገ ጥራት ፣ቅልጥፍናና ግልፅነት ያለው መልካም የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን ለማድረግ የተቋቋመና ዜጎች አስተዳደራዊ በደል ሲደርስባቸው በህገ መንግስቱ መሰረት አቤቱታቸውን በማቅረብ መርምሮ መፍትሄ እንዲያገኙ እየሰራና እንዲሁም አስፈፃሚ አካላት ላይ አገልግሎታቸውን በህገመንግስቱ መሰረት እያከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ ቁጥጥርና የጥናት ስራዎችን በማከናወን አመርቂ ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል፡፡

ምንም እንኳን በአገራችን መልካም አስተዳደር በአሁኑ ወቅት የሞት ሽረት ጉዳይ ቢሆንም በአንድ ጊዜ የሚቋጭ ጉዳይ እንዳልሆነ የብዙ አገራት ተሞክሮዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም ዜጎች የመልካም አስተዳደር ጉዳይ የኔ ጉዳይ ነው በማለት የሕግ የበላይነትንና መልካም

አስተዳደርን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ብልሹ አሰራሮችን፣ ሙስናን፣ አስተዳደራዊ በደሎችንና አድልዎችን በማጋለጥ ከተቋሙ ጎን በመቆም የዜጎችን ህገመንግስታዊ መብት ለማረጋገጥና የመብታቸው ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ሲጋሩ ይገባል፡፡

መልካም አስተዳደር በዋነኛነት ስምንት መርሆዎች አሉት፡፡ ከመርሀዎች ውስጥ አንዱ ግልፅነት ነው፡፡ ይህ መርህ መረጃ ለዜጎች በነፃነት የሚደርስበትን እንዲሁም ህግና ስርዓትን በተከተለ አግባብ በጉዳዮቻቸው ላይ ተወያይተው ውሳኔ ማሳለፍ የሚችሉበትን አግባብ ይገልፃል፡፡ በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የመገናኛ ብዙሀንና የመረጃ ነፃነት ህግ ለመደንገግ የወጣው አዋጅ 590/2000 ክፍል ሶስትን በማስተግበር ዜጎች መረጃ እንዲያገኙ እየሰራ ይገኛል ፡፡ ከግልጽነት ጋር ተያይዞ መረጃ ለዜጎች በነፃነት እንዲደርስ ከሚያስችሉ ዘዴዎች ውስጥ ሚዲያዎችና የህትመት ውጤቶች ሰፊ ድርሻ እንደሚይዙ በዘርፉ ምሁራን የተሰሩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

ተቋሙ በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችና የህትመት ውጤቶች አማካይነት ለዜጎች ተገቢውን መረጃ በማቅረብ፣ የዜጎችን ግንዛቤ በማሳደግ፣ የመንግስት ፖሊሲዎችና እስትራቴጂዎችን ይፋ በማድረግ፣ አዋጆችና የሕግ ማዕቀፎችን ማሕበረሰቡ እንዲያውቃቸው ተከታታይነት ያላቸው ስራ በመስራት የዜጎችን ግንዛቤ እንዲዳብርና የሚደርስባቸው አስተዳደራዊ በደሎች አቤት በማለት መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን እንዲያስከብሩ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ተቋሙ መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ ሊነጣጠሉ የማይችሉ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታዎች እንደሆኑና ለመልካም የመንግስት አስተዳደር ዘላቂነት ከሕዝብ ቁጥር እና ፍላጎት ጋር የተገናዘበ ምላሽ ሰጪ አካል እንደሚያስፈልግና የፈፃሚ አካላት የመፈፀም አቅም ክፍተት፣ የግልፀኝነት ችግር፣የመልካም አስተዳደር ጉዳይ የጋራ እና የሁላችንም ድርሻ እንደሆነ ባለመገንዘብ ኃላፊነት ያለመውሰድና ወቅታዊ ፖሊሲዎችን መሰረት ያደረገ ቅንጅታዊ አሠራር ያለመኖር በመልካም አስተዳደር ግንባታ ላይ ችግር እየፈጠረ በመንግስትና ህዝቡ መካከል የጋራ መግባባት እንዳይፈጠርና በሚተገበሩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ደንቃራ እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ስለዚህ አስፈፃሚ አካላት ወቅቱንና የህዝቡን ፍላጎት በመረዳትና ግልፅና ቀልጣፋ አሰራርን በመዘርጋት መልካም የመንግስት አስተዳደር ማስፈን ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመጨረሻም የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም መልካም አስተዳደርን የማስተገብር ሃላፊነት ተሰጥቶት እየሰራ ያለ እንደመሆኑ ፈፃሚ ኣካላት ዜጎችን እንዳይበድሉ፣ ዜጎችም መልካም አስተዳደር የሁላችንም ጉዳይ እንደሆነ አውቀው በደል ሲደርስባቸው ሕገ-መንግስታዊ መብታቸውን አሟጠው በመጠቀም ተሟጋች እንዲሆኑና መልካም የመንግስት አስተዳደርን በዘላቂነት በማስፈን ሂደት ውስጥ የበኩላቸውን ድርሻ ሊወጡ እንደሚገባ፣ የሚዲያ ተቋማትና የህትመት ውጠቶች የአስተዳደር

በደሎችን ነቅሶ በማውጣትና ሲከሰቱ በማጋለጥ ብሎም በመልካም አስተዳደር ላይ ዜጎችን በማወያየት ግብዓት ወስደው ለመንግስት ቀጣይ የልማት ፖሊሲ እና እስትራቴጂ አቅጣጫ በማመላከት አገራችንን ከሙሰኞች እና ከመልካም አስተዳደር እጦት ታድገው የልማትና ዴሞክራሲ አምባሳደሮች እንዲሆኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## ቀልድና ቁም ነገር

### አባትና ልጅ

አባትና ልጅ ሆነው መንገድ ሲሄዱ አባት በቅሎ ላይ ሆኖ ልጅ ደግሞ በቅሎውን እየጎተተ ሲሄዱ ሳለ ሰዎች አይተዋቸው የዛሬ ዘመን አባት ለልጁ አይሆንም ይሄ ትንሽ ልጅ በቅሎ እያስጎተተ እሱ በቅሎ ላይ ይንቀባረራል ይላሉ አባት ይህንን ይሰማና ናልጄ አንተ በቅሎ ላይ ውጣ እኔ እጎትታለሁ ይላል ቀጣይ መንደር ሲደርሱ የሰፈሩ ሰዎች የዛሬ ዘመን ልጅ አባቱን አያከብር እሱ በበቅሎ እየሄደ አባቱን ያስጎትታል ይላሉ ይህንን ሲሰሙ እስቲ አሁን ሁለታችንም በቅሎ ላይ እንውጣ ተባብለው ሁለታቸውም በቅሎ ላይ እየሄዱ ሳለ የመንደሩ ሰዎች እንዴት በቅሎ ላይ ሁለት ይቀመጣሉ ሰው ለእንስሳት ማዘን አቆመ ይላሉ፣ ይህን ሲሰሙ እስቲ አሁን ሁለታችንም በእግራችን እንጓዝ ብለው በቅሎውን መጎተት ጀመሩ በዚህ ጊዜ የሰፈሩን ሰዎች የምንሞኝ ናቸው በቅሎ እያላቸው በግራቸው ይሄዳሉ እያሉ ይሳለቁባቸዋል፡፡

- ሰው ምንም ነገር ብታደርግ የምታደርገው ነገር ሳይጥመው ይችላል ስለዚህ የምታደርገውን ካመንክበት የሰዎችን አስተያየት መጠየቅ ተገቢ አይሆንም ትክክል ነው ብለህ ያመንክበትን ከማድረግ ወደኋላ አትበል፡፡

## ባሳገሩ

............

ከዕለታት አንድ ቀን በአንድ አነስተኛ የገጠር መንደር የሚኖር ሰው ልጁን ለውሻው አስጠብቆ ለጉዳይ ራቅ ወዳለ ቦታ ይሄዳል ውሻ ልጅ እየጠበቀ ሳለ ዘንዶ ቤት ይመጣል በዚህ ጊዜ ውሻው ከዘንዶ ጋር ትግል ይገጥማል ልጅ ቢጮህም የሚሰማ የለም ውሻ ታግሎ ዘንዶውን በመንከስ ገድሎ ልጁን አደና ውጭ ተኝቶ ሳለ አባት ይመለሳል ውስን ሲመለከት አፉ ላይ ደም በደም ሆኖ ሲመለከት ልጄን በልቶ ጭራውን ያወዛውዛል እንዴ በማለት ሽጉጡን በማውጣት ተኩሶ ይገድለዋል ፡፡ ቤት ሲገባ ልጁ ተኝቶ ልጁን ሲበላ የመጣው ዘንዶ ሞቶ ይመለከታል፡፡

### አስር አለቃን አዝላ የምትፈጨው ሚስት

የሴትዬዋ ውሽማ አስር አለቃ ባል ሲወጣ ጠብቆ ይገባል ከእለታት አንድ ቀን ባጋጣሚ ቀን ላይ ባልም ያምረውና ስራ ጥሎ ይመጣል ሲጣራ አትመልስም ልጁን ጠርቶ እስቲ እናትህን ጥራት ይለዋል እሷም መጣሁ ብላ ትቀራለች በኃላ እስቲ ምን እንደምታደርግ አይተህና ይለዋል በዚህ ጊዜ ልጅ አይቶ መጥቶ አስር አለቃን አዝላ እየፈጨች ነው አለው ይባላል፡፡

### የህዝብ ተሳትፎ

- ሂድ- ህዝብን ፈልግ
- ከነሱ ተማር
- አብረህ አቅድ
- አብረህ ፈፅም
- አገልግል
- እነሱ ባላቸው ላይ ጀምር
- እውቀታቸውን አስፋፉ

## እንቆቅልሽ

1.ሁለት አባትና ሁለት ልጆች የዳክዬ አደን ወጥተው ሁሉም ገድለው ይዘው መጥተው ለሚስቶቻቸው ይሰጣሉ ማታ ተሰርቶ ለራት ሲቀርብ 3 ይሆናሉ አንዱ ዳክዬ የት ሄደ?

2. ፍየል፣ ነብርናጎመን አንድ ሰው ይዞ ሲጓዝ ወንዝ ያጋጥመዋል። ሰውዬው ከሌለ ነብር ፍየልን ይበላዋል ፍየል ደግሞ ጎመንን ይበላዋል አንድ ላይ ማሻገር አይችልም ስለዚህ እንዴት ያሻግራቸው?

## Qutations

-Change is the law oflife.and those who look only the past or present are certain to miss the future.

-The simplest and the shortest ethical percept is to be served as little as possible and to serve others as much as possible.

-Accept every thing about yourself.i mean every thing,you are you and that is the begning and the end. No apologise,no request.